የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ሁለተኛ ዓመት ቁጥር ፩
አዲስ አበባ ጥቅምት ፳፬ ቀን ፪ሺ፰ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

22nd Year No. 1
ADDIS ABABA, 4th Novemberr,2015

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፫፻፵፱/፪ሺ፰

ቦንጋ ዩኒቨርሲቲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ................................................ ገጽ ፰ሺ፭፻፷

Council of Ministers Regulation No.349/2015

Bonga University Establishment Council of Ministers Regulation ---------------------------------------Page 8560

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፫፻፵፱//፪ሺ፰ ዓ.ም

## የቦንጋ ዩኒቨርስቲን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፱፻፲፮/፪ሺ፰ አንቀጽ ፭ እና ፴፱ እና በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር ፮፻፶/፪ሺ፩ አንቀጽ ፭(፩) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "የቦንጋ ዩኒቨርሲቲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፫፻፵፱/፪ሺ፰" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. መቋቋም**

፩/ የቦንጋ ዩኒቨርሲቲ (ከዚህ በኋላ "ዩኒቨርሲቲ" እየተባለ የሚጠራ) ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋም ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡

፪/ የዩኒቨርስቲው ተጠሪነት ለትምህርት ሚኒስቴር ይሆናል፡፡

COUNCIL OF MINISTERS REGULATION No.349/2015

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO PROVIDE FOR THE ESTABLISHMENT OF BONGA UNIVERSITY

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 and 39 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 916/2015 and Article 5(1) of the Higher Education Proclamation No. 650/2009.

**1. Short Title**

This Regulation may be cited as the "Bonga University Establishment Council of Ministers Regulations No. 349/2015".

**2. Establishment**

1/ Bonga University (hereinafter the "University") is hereby established as an autonomous higher education public institution having its own legal personality.

2/ The University shall be accountable to the Ministry of Education.

፫/ ዩኒቨርሲቲው በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር ፮፻፶/፪ሺ፩ እና በፌደራል ዩኒቨርሲቲዎች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፲/፪ሺ፫ መሠረት ይተዳደራል፡፡

**፫.ዋና ግቢ**

የዩኒቨርሲቲው ዋና ግቢ በቦንጋ ከተማ ሆኖ በሌሎች ቦታዎች የትምህርት ክፍሎች እና የምርምርና የሕብረተሰብ አገልግሎት ማዕከሎችን ሊያቋቁም ይችላል፡፡

**፬.ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ቀን ጥቅምት ፳፬ ቀን ፪ሺ፰ ዓ.ም**

**ኃይለማርያም ደሳለኝ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

3/ The University shall be governed by the Higher Education Proclamation No. 650/2009 and the Federal Universities Council of Ministers Regulation No. 210/2011.

**3. Main Campus**

The University shall have its main campus at Bonga Town and may establish elsewhere other academic units and centers of research and community services.

**4. Effective Date**

This Regulation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, this 4th day of November, 2015.**

**HAILEMARIAM DESALEGN**

**PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት